**በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ዙሪያ**

**ከባለድርሻ አካላት ግብዓት ለመሰብሰብ የተዘጋጀ የውይይት መድረክ**

**<u>የቡድን ውይይቱ አላማ፣ መርሆዎችና የመወያያ ጥያቄዎች</u>**

| **አጠቃላይ: የውይይቱ አላማና መርሆች** |
|---|

- ቢሆንም፣ ይህንን ምክክር ያዘጋጀው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አዘጋጅ ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን ነው። ይህ ቡድን ገለልተኛ እና ራሱን ችሎ የሚንቀሳቀስ ከመሆኑም በተጨማሪ ለማንኛውም ውስጣዊና/ውጫዊ ጫና ወይም ተጽእኖ ተጋላጭ አይደለም።
- የቡድን ውይይቱ አላማ በቀረቡት አማራጮች ላይ ጠለቅ ያለ ውይይት በማድረግ ግብዓት መሰብሰብ ነው። ስለሆነም ተወያዮች በውይይት ጊዜ ለመነሻነት የቀረቡትን ጥያቄዎች እንደ መነሻ በመውሰድ ሀሳባቸውን ማንሸራሸር ይችላሉ።
- ተሳታፊዎች የቀረቡ አማራጮች እና መነሻ ሀሳቦች ላይ ያሏቸውን ምልከታዎች፣ ከነምክኒያቶቻቸው እንዲያስረዱ፣ አማራጭ መሆን የለባቸውም የሚሏቸውን እንዲጠቅሱ፣ ጠንካራ ጎኖች እና ተግዳሮቶቹን በመመልከት እንዲያጎለብቱ በነፃ የውይይት መንፈስ እንዲመካከሩ ይበረታታሉ።
- የቀረቡት አማራጮች ለውይይት መነሻነት እንጂ፣ ብቸኛ እና ለሌሎች አማራጮች እድል በማይሰጥ ዝግ በሆነ አግባብ ስላልሆነ፣ ተወያዮች እንደ አማራጭ ያልተካተቱ እና መካተት ይገባቸዋል የሚሏቸዉን አማራጮች ከነምክኒያታቸው እና ፋይዳቸው እንዲያነሱ ይበረታታሉ።
- በዉይይቱ ሂደት የተሳታፊዎችን፣ የአመቻቾችን እና የሌሎችን ግለሰቦች ክብር እና ስብዕና በሚያከብር መልኩ ይሳተፉ።
- የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች የሁሉንም ሰው አስተያየት ቢስማሙም፣ባይስማሙም በማክበር ማዳመጥ ይኖርባቸዋል።
- በውይይቱ ወቅት ተሳታፊዎች በፆታ፣ በብሔር ማንነት፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በሌላ ምክንያት ጥቃትን የሚቀሰቅሱ አስተያየቶች፤ንግግሮችን፣ ጥላቻ አዘል ወይም መድሏዊ አነጋገሮች መጠቀም የለባቸውም።
- ሌሎች ተሳታፊዎች ሲናገሩ ባለማቋረጥ በተገቢዉ ሁኔታ ያዳምጡ፤ ሃሳባቸውንም ገልፀው እንዲጨርሱ ይፍቀዱላቸው።
- የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አዘጋጅ ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን የተሳታፊዎችን አስተያየቶች የሚጠቀምበትም ሆነ በተለያዩ ጽሁፎች ዉስጥ ሀሳቦቹን የሚጠቅሱት የተሳታፊዎችን ሚስጥራዊነት በሚያከብር እና ጉዳት በማያደርስመልኩ ነዉ። በምንም አይነት ሁኔታ የተሳታፊዎች አስተያይቶች ጋር በተያያዘ ስማቸው አይጠቀስም። በመሆኑም ተሳታፊዎች ይህን ብናገር ጉዳት ይደርስብኛል የሚል ስጋት ሳይኖራቸው ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ ይበረታታሉ።
- በዉይይቱ ሂደት የሁሉም የቡድን አባላት የነቃ ተሳትፎ በጣም የሚበረታታ ነው። በመሆኑም እያንዳንዱ የዉይይቱ ተሳታፊ ለሁሉም የመወያያ ጥያቄዎች አስተዋጽኦ እንዲያደርግ በማሰብ በቂ የመወያያ ጊዜ ተመድቧል።.
- ለቡድን ዉይይቱ ሶስት ሰዓት ተመድቡዋል።
- ለያንዳዱ ቡድን አንድ አመቻች/አሳላጭ (facilitator) እና አንድ ማስታውሳ ያዥ (note taker) በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አዘጋጅ ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን ይመደባል።

| ማስታወሻ፡ ለአመቻቾች/አሳላጮች |
|---|

- እባክዎንከላይ የተመለከቱትን የውይይቱ አላማ እና መርሆች ውይይቱ ከመጀመሩ በፊት ለተውያዮች ይግለጹ/ያስረዱ።
- ለቡድን ውይይቱ የተሰጠዉን የመወያያ ጊዜን በቅደሚያ ያሳውቁ።
- ከዚያም በማስከተል በቡድን ወይይቱ የተነሱትን አንኳር እና ቁልፍ ሃሳቦች ላይ በጋራ ውይይት እንደሚኖር ለተሳታፊዎች በማሳወቅ፣ ለዚሁ ተግባር ከተወያዮች አንድ አቅራቢ ያስመርጡ።

- ከታች የተዘረዘሩትን የመወያያ ጥያቄዎች አንድ በአንድ ለተወያዮች በማንበብ ውይይቱን ያሳልጡ።
- ሁሉም የቡድን ዉይይቱ ተሳታፊዎች በንቃት እንዲሳተፉ ያበረታቱ።
- በውይይት ሂደቱ የማብራሪያ ወይም የማጣሪያ ጥያቄ እንደ አስፈላጊነቱ ይጠይቁ።
- መሪ ጥያቄ (leading question)) መጠያቅ የተከለከል ነዉ
- ውይይቱ በተመደበው ጊዜ ዉስጥ እንዲጠናቀቅ ያድርጉ።

| ማስታወሻ፡ ለማስታወሻ ያዥ |
|---|

- በተወያዮች የሚነሱተን ሀሳብ እና አስተያየቶች በተገቢዉ መልኩ ማስታወሻ በመያዝ ይመዝግቡ።
- የተወያዮችን ፍቃደኝነት በመጠየቅ፣ የቀረጻውን አላማ በግልጽ በማስረዳት፣ እንዲሁም የተወያዮች ማንነት እንደማይገለጽ በማስረዳት፣ ውይይቱን በመቅረጸ ድምጽ ይቅረጹ።
- ተወያዮች የተመደበዉን ጊዜ በአግባቡ እንዲጠቀሙ በማስታወስ ለውይይቱ የተሰጠዉን ጊዜ ይቆጣጠሩ።
- በውይይቱ በተገቢዉ መንገድ በቂ ውይይት ያልተደረገበት ወይም የተዘለለ ጥያቄ ወይም የጠራ ግብዓት ያልተሰጠበት ካለ፣ጥያቄውን በማስታወስ ውይይት እንዲደረግበት ሀሳብ ያንሱ።
- በውይይቱ የተነሱተን ነጥቦች እና ሀሳቦች በተገቢዉ መንገድ በመሰነ፣ የተወያዮቹን ሀሳብ እና አስተያየቶችን ብቻ እንጂ የማስታወሻ ያዥን የግል ምልከታ/ሀሳብ ሳይሆን ፣ አመቻቹ/አመቻቹዋ በማስታወሻዉ ላይ ያለዉን/ያላተን ሀሳብ/ አስተያየት በማካተት ለሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አዘጋጅ ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ያስረክቡ።

**1. የወንጀል ተጠያቂነት እንደ ሽግግር ፍትህ አማራጭ**

የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ሊኖር ይገባል?

- **አማራጭ አንድ፡** ጉልህ የሆኑ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ውይም ከባድ ወንጀሎች ላይ ያተኮረ የክስ ሂደት ማከናወን (ጉልህ የሰባዊ መብቶች ጥሰቶች ማለት ከባድ ፣ መጠነ ሰፊ ወይም ስለታዊ የሰባዊ መብቶች ጥሰቶች ማለት ሲሆን ጥሰቶቹም በስብዕና ላይ የሚፈጸሙ ውንጀሎች፣ የጦር ወንጀሎች፣ ዘር ማጥፋት፣ ቶርቸር፣ እና የመሳሰሉተን ከባድ አለም አቀፍ ወንጀሎች የሚያካትቱ ናቸዉ)
- **አማራጭ ሁለት፡** ሁሉንም አይነት የሰብዓዊ መቶችት ጥሰት ወይም ሁሉንም ወንጀሎችን ያካተተ የክስ ሂደት

በየትኛዎቹ አጥፊዎች ላይ ክስ ሊመሰረት ይገባል?

- **አማራጭ አንድ፡** ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት ባላቸው አጥፊዎች ላይ (ማለትም ጠንሳሾች፣ትእዛዝ የሰጡ፣ ያቀዱ፣ የመሩ እና ከፍተኛ ሀላፊነት ኖሮባቸው ሀላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ምክንያት ጉዳት እንዲደርስ ያደረገ
- **አማራጭ ሁለት፡** የወንጀል ክስ ሂደቱ በማንኛውም ደረጃ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች ውስጥ የተሳተፉ ሰዎችን በማካተት የሚከናወንበት አማራጭ

ክሶቹን የሚመለከቱት ፍርድ ቤቶችን በሚመለከት፡

- **አማራጭ አንድ፡** በከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውስጥ ተገቢዉን ልየታ በማድረግ (ማለትም በብቃታቸው፣ የትምህርት ዝግጅታቸው፣ልምዳቸው እና ሙያዊ ታማኝነታቸው ብቁ የሆኑትን በመመደብ) ልዩ ችሎት በማቋቋም ክሶቹን በመስማት ውሳኔ መስጠት
- **አማራጭ ሁለት፡** ልዩ ፍርድ ቤት በማቋቋም ክሶቹን በመስማት ውሳኔ መስጠት
- አማራጭ ሶስት፡ ሌላ ...............

ምርመራ እና ክስን የሚያከናውኑ ተቋማትን በሚመለከት፡

- **አማራጭ አንድ፡** ባለው የፖሊስ እና የዐቃቤ ህግ ውስጥ ተገቢዉን ልየታ በማድረግ የተለየ ቡድን በመመስረት
- **አማራጭ ሁለት፡** አሁን ካለው የዓቃቤ ሕግ ተቋማት ውጪ ሌላ ምርመራና የክስ ሂደቶችን የሚያስተባብር ልዩ (ነጻና ገለልተኛ) የዓቃቤ ሕግ ተቋም በማቋቋም የፖሊስ እና የምርመራ ባለሙያዎችን በመመደብ
- አማራጭ ሶስት፡ ሌላ ……………

**2. እውነትን ማፈላለግና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት**

እውነትን የማጣራትና እርቅን የሚመለከቱ ተግባራት ለየትኞቹ ገዳዮች እና ጥሰቶች ሊተገበሩ ይገባል? (ሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፣ የተወሰኑ ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ለምሳሌ የሲቪልና ፖለቲካዊ ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ወዘተ)

እውነትን ማፈላለግና እርቅን ማውጣት ሂደቱን በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?

- አማራጭ አንድ፡ አዲስ በሚቋቋም የሀቀ አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት
- አማራጭ ሁለት፡ በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
- አማራጭ ሶስት፡ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት
- አማራጭ አራት፡ ሌላ ……………

**3. በቅድመ ሁኔታ የሚሰጥ ምህረት እንደ ሽግግር ፍትህ አማራጭ**

የምህረት ቅድመ ሁኔታዎችን በሚመለከት

- ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ እና የማያደርጉ መስፈርቶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?[1]

ምህረት የመስጠቱን ሂደት በየትኛው ተቋም ማከናወን ይገባል?

- አማራጭ አንድ፡ አዲስ በሚቋቋም የሀቀ አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት
- አማራጭ ሁለት፡ በአዋጅ ቁጥር 1089/2018 መሰረት በተቋቋመው የምህረት ቦርድ
- አማራጭ ሶስት፡ ሌላ ……………

**4. ማካካሻ እንደ ሽግግር ፍትህ አማራጭ**

የማካካሻ ስርአቱ

- የትኛዎቹ ተጎጂዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል
- ምን አይነት የማካካሻ ስርአቶችን ቅድሚያ በመስጠት መተግበር ይገባል፡ (መልሶ ማቋቋም፣ ካሳ (ግለሰባዊ፣ የጋራ)፣ ማገገሚያ ወዘተ)

የማካካሻ ስርአቱን የትኛው ተቋም ይምራው/ ያስተባብረው?

- አማራጭ አንድ፡ የግል ካሳን ጉዳይ በመደበኛው የህግ ስርአት በፍርድ ቤቶች እንዲታይ ማድረግ
- አማራጭ ሁለት፡ አዲስ በሚቋቋም ኮሚሽን አማካኝነት
- አማራጭ ሶስት፡ በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
- አማራጭ አራት፡ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት

**5. ተቋማዊ ማሻሻያ በሚመለከት የሚከናወኑ የመለየት እና ማጥራት ተግባራት እንደ ሽግግር ፍትህ አማራጭ**

- የትኞቹን ተቋማት ቅድሚያ በመስጠት የመለየት እና ማጥራት ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል
- ተመሳሳይ ወንጀሎች እና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ ምን ምን እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው?

የተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራቱ በማን ይከናወናሉ?

- አማራጭ አንድ፡ የተቋማትን ለውጥ የሚያስተገብር የልየታ፣ የማጥራት እና ከስራ የማግለል ስልጣን የተሰጠው ገለልተኛና ነጻ የሆነ አካል በማቋቋም ተግባራቶቹን ማከናወን፡
- አማራጭ ሁለት፡ በሁሉም ተቋማት ውስጥ የልየታ፣ የማጥራት እና ከስራ የማግለል ሀላፊነት ያላቸው ቡድኖች በማዋቀር ተግባራቶቹን ማከናወን

[1] ለምሳሌ ያህል ከበዳዮች የተሳተፎ ደረጃ፣ ከተጠረጠሩበት ወይም ከፈጸሙት ወንጀል አንጻር፣ በዳዮች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች (ማለት እውነቱን መናገር፣ መጸጸት፣ ይቅርታ መጠየቅ ወዘተ) አንጻር።

- አማራጭ ሶስት፡ ሌላ ...............

**6. የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከየትኛው ጊዜ ይጀምር?**

- **አማራጭ አንድ፡** ከ1983 በፊት ያሉትን ጉዳዮች በሚያካትት አግባብ
- **አማራጭ ሁለት፡** ከ1983 ጀምሮ
- **አማራጭ ሶስት፡** ከ1987 ጀምሮ
- **አማራጭ አራት፡** ከ2010 ጀምሮ
- አማራጭ አምስት፡ ለክስ ጉዳይ 1987 ጀምሮ፣ ለእውነት ማፈላለግ፣እርቅ ማስፈንና ማካካሻ ጉዳይ ግን መረጃ እና ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ
- አማራጭ ሶስት፡ ሌላ

**7. የባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቶች በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ምን ሚና ሊኖራቸው ይገባል?**

- አካባቢያዊ ወይም ሀገራዊ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ተለይተው ሊጠቀሱ የሚችሉ ባህላዊ አሰራሮች፣
- የትኞቹን ጉዳዮች ለመፍታት እራሳቸዉን ችለው ወይም ከየትኞቹ የሽግግር ፍትህ አላባ/ዎች ጋር ሊተገበሩ እንደሚገባ ያብራሩ፣
- እነዚህን ባህላዊ ዘዴዎች እና እሴቶች በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይ ለመጠቀም በስረአቶቹ ላይ መደረግ የሚገባቸዉ ለዉጦች ወይም ማሻሻያዎች ካሉ ይጥቀሱ

**8. በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ክልሎችና የከተማ መስተዳደሮች ሊኖራቸው የሚችለውን ሚና በሚመለከት?**

- ምን ሚና ሊኖራቸው ይገባል? (ከብሄራዊ የሽግግር ፍትህ መርሃግብሩ ጋር መተባበርና የተለያዩ ድጋፎችን ማድረግ፣ የራሳቸዉን የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር ወዘተ)